# ፈይሳ ጃታ... ብሄራዊ ውርደትን ያልተቀበለ ጀግና!!

ሰሞኑን ስለብሄራዊ ውርደት ብዙ ይባላል። ብዙ ስለሚባለው ነገር መልሼ ከማውራት ይልቅ፤ አንድ ሰው ላስተዋውቃቹሁ። ፈይሳ ጃታ ይባላሉ። ሀረር ውስጥ ለብዙ አመታት የኖሩ ናቸው። ጣልያን የጫነብንን ብሄራዊ ውርደት ያልተቀበሉ፤ የሱማሌ ወረራን ተከትሎ የመጣውን ሽንፈት፤ "እምቢኝ" ያሉ ጀግና ነበሩ።

የሀረሩን ፈይሳ ጃታ ያለ ምክንያት አላነሳሁዋቸውም። "ብሄራዊ ውርደት" ብለን በምንጠራቸው ዘመኖች፤ እንደሳቸው አይነት ያለተዘመረላቸውና ምንም ያልተባለላቸው ሰዎች መኖራቸውን ለማስታወስ፤ ከዚያም አልፎ ሁሌ ብሄራዊ ውርደትን ያሸነፉ፤ ጀግኖች መኖራቸውን ማውሳት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

ለነገሩ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በበርካታ የታሪክ ምዕራፎች ብሄራዊ ውርደትን አስተናግደናል። አንደኛውና ሁላችንም የምናውቀው በጣልያን ወረራ ወቅት፤ በራሳችን ባንዳዎች የተፈጸመብን ውርደት ነው። ሁለተኛውን ውርደት የተከናነብነው በቀይ ሽብር ዘመን ወንድም ወንድሙን ገድሎ የፎከረበት ወቅት ሲሆን፤ ሶስተኛው ብሄራዊ ውርደት ደግሞ፤ አሁን በአገራችን ያለው ስርአት ያከናነበን የቅሌት ቡሉኮ ነው። በመግቢያዬ ላይ እንደገለጽኩት ስለያንዳንዱ ዘመን ብሄራዊ ውርደት ለመተንተን አይደለም - የዛሬ መነሻዬ። ይልቁንም በእንደዚህ አይነት የውርደት ዘመናት አንገታቸውን ቀና አድርገው፤ ሰንደቅ አላማችንን ከፍ ስላደረጉ አንድ ግለሰብ ጥቂት ለማለት ፈልጌ ነው።

## ተራኪ - ተስፋ ጥ ዑመ-ልሣን
## ጸሃፊ - ዳዊት ከበደ ወየሳ

እንደገና ላስተዋውቃቹህ። ፈይሳ ጃታ ይባላሉ። ፊታቸው ሁሌም ሙሉ ጺም ያለው፣ ቀጭን፣ ቁመታም፣ ሁሌ ቁምጣ የሚያደርጉ ቆፍጣና ሰው ናቸው። በጣልያን ዘመን ገና ወጣት ልጅ ነበሩ። የተወለዱት ሰላሌ አውራጃ ሲሆን፤ ኩሩ ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ናቸው። በወቅቱ የአርበኝነት ዘመን የአካባቢው ወጣቶች ይሰለፉበት በነበረው የጃጋማ ኬሎ ጦር ስር ሆነው ለአገራቸው ክብር ከቆሙት መካከል አንዱ ነበሩ።

በዚህ የአርበኝነት ዘመን እሳቸው የነበሩበት ጦር፤ ጣልያንን ለመምታት እና ግዳጁን ለመወጣት ወደ ሰላሌ ያመራል። እዚያ ሲደርሱ ግን፤ የሰላሌ አካባቢ ዋና ሃላፊ ወይም ባንዳ ሆነው ለጣልያን አገልግሎት ይሰጡ የነበሩት የእናታቸው ወንድም፤ አጎታቸው መሆኑን ይሰማሉ። ቀጥሎም ወደ ከተማ ገብተው ይህንኑ በአይናቸው አይተው ያረጋግጣሉ። የአካባቢው ኦሮሞዎች ከጣልያን ጦር ባልተናነሰ፤ የፈይሳ አጎት ይፈጽሙባቸው የነበረው በደል ከባድ መሆኑን ተመለከቱ። በሁኔታው አዝነው፤ ከአጎታቸው ጋር ጦርነት ላለመግጠም ብለው፤ እንዳዘኑ ያቺን መንደር ለቀው ወጡና በሌላ መስመር በአርበኝነት አገለገሉ።

ጣልያን ድል ከተመታ በኋላ አርበኞች ወደ አገራቸው ሲመለሱ፤ አጎታቸው የባንዳነት ቡሽ ኮፍያቸውን አውልቀው፤ ጃንሆይ የሰጧቸውን አዲስ የስልጣን ካባ ደርበው... አሁንም ከድል በኋላ ህዝቡን ሲያተራምሱት ተመለከቱ። በጣልያን ጊዜ የነበረው ብሄራዊ ውርደት ሳያንስ፤ ከድል በኋላም ተጨማሪ ውርደትን ለመሸከም ትከሻቸው አልቻለም፤ ከህሊናቸው ጋር ሙግት ገጠሙ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ አንድ ቀን፤ አጎታቸው እንደተለመደው በቅሎ ላይ ሆነው ገበያተኛውን ሲያምሱት፤ የሚታሰረውን ሲያስሩና ሲያሳስሩ አይተው አዘኑ። በዚህን ጊዜ "ሁለት ጊዜ አንዋረድም! ሞትም አንዴ ነው!" ብለው፤ የራሳቸውን አጎት በጥይት መትተው ገደሏቸው።

ከዚህ በኋላ ፈይሳ ጃታ ሰላሌን ለመጨረሻ ጊዜ ለቀው ወጡ። የሰላሌው የታሪክ ምዕራፍ ተዘጋና ሌላኛው የታሪካቸው ምዕራፍ ሀረር እና ጅጅጋ ላይ ተጀመረ። በኋላ ላይ ብሄራዊ እርቀ ሰላም ለማውረድ ሲባል መንግስት የምህረት አዋጅ አወጀ። "ነፍስ ያጠፋህ በሙሉ፤ እጅህን ሰጥተህ ታርቀህ በሰላም ኑር።" ተባለ። ፈይሳ ጃታም አዋጁን ተከትለው፤ ምህረት ተደርጎላቸው እንደማንኛውም ሰው ከጅጅጋ 30 ኪሎ ሜትር ርቀት በሚገኘው ፋፈም ላይ መሬት ተመርተው መኖር ጀመሩ።

ከጊዜ በኋላ ግን... ፈይሳ ጃታ የተመሩበት መሬትት ውስጥ ለውስጥ የፋፈም ወንዝ ይሄድበት ኖሮ፤ ሚስጥሩ ሲታወቅ የወቅቱ ባለስልጣናት ይዞታው ላይ አይናቸውን ጣሉ። ከነዚያ ባለስልጣናት መካከል አሁን ስማቸውን መጥቀስ የማልፈልጋቸው፤ ፖሊስን ማዘዝ የሚችሉ ጄነራል ነበሩ። ጄነራሉ ፈይሳ ጃታ መሬቱን እንዲለቁ ቢያስጠይቋቸው "አሻፈረኝ" አሉ። ሽማግሌዎች ቢላኩም፤ "ሬሳዬን ተሻግሮ ይውሰድ" ብለው መለሷቸው። በኋላ ላይ እንዲያዙ ፖሊስ ተላከ።

ፈይሳ ጃታም፤ "በህግ አምላክ፤ ይዞታዬ ውስጥ አትግቡ!" ብለው አስጠነቀቁ። ፖሊሶቹ ግን የሚሰሙ አልሆነም። በመጨረሻ ሁለቱን ፖሊሶች ገደሉ። ፈይሳ ጃታ ፖሊሶቹን ገድለው፤ ለተወሰነ ግዜ ከፖሊስ ጋር ድብብቆሽ ይጫወቱ ጀመር። የአጋጣሚ ነገር ሆነና፤ በ1953 ዓ.ም. ጄነራሉ በጃንሆይ ላይ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ በማድረግ ጥፋት ተወንጅለው ተገደሉ። ከጄነራሉ ሞት በኋላ... ለፈይሳ ጃታ ለሁለተኛ ጊዜ ምህረት ተደረገላቸው።

በዚህ መሃል ያለውን ታሪክ እንለፈውና ወደ ሱማሊያ ወረራ ዘመን ልውሰዳቹህ። በየካቲት ወር 1969 ዓ.ም. የሱማሊያ ወረራ ወቅት፤ ሱማሌዎች ጎዴ፣ ቀላፎ፣ ቀብሪዳሃር፣ ደገሃቡር፣ ዋርዴር የሚባሉት ከተሞችን ያዙ። ሃምሌ ላይ ደግሞ ጅጅጋን ለመያዝ ትልቅ ጦርነት ተከፈተ። በወቅቱ ፈይሳ ጃታ እድሜያቸው ወደ እርጅናው ተጠግቶ ነበር። እንደዚያም ሆኖ ህዝቡን ለማስተባበር ጉልበታቸው አልደከመም፤ አንደበታቸው አልታሰረም።

ሃምሌ 8 ቀን፣ "ከሱማሌ ጋር ተባብራችኋል" የተባሉ ሰዎች ተገደሉና በጅጅጋ ትልቅ ፍጅት ሆነ። በሳምንቱ የሱማሌ ጦር እየገፋ ሲመጣ፤ ህዝቡ ተስፋውን በኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ላይ ጥሎ ነበር። ሆኖም የጅጅጋ ከተማ ከመያዟ አንድ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ከየወረዳው አፈግፍጎ የመጣው የጦር ሰራዊት አባላት፤ ለሊቱን ቤተሰባቸውን ይዘው አካባቢውን ለቀው፤ ጉዟቸውን በመኪና እና በእግር ወደ ሃረር አደረጉ።

በንጋታው ጠዋት የጅጅጋ ህዝብ ከእንቅልፉ ሲነሳ፤ ከተማው ዙሪያውን በሱማሌ ታንክ ተከቦ ተመለከተ። በየጋራው ላይ በርካታ የሱማሌ ታንክ አፈ ሙዙን ወደ ከተማው አድርጎ ቆሟል። የጅጅጋ ህዝብ በሁኔታው ተደናገረ። ለሊቱን ሲከናወን ስለነበረው ሁኔታ ብዙም የሚያውቀው ነገር አልነበረም። የኢትዮጵያ ጦር አካባቢውን ለቅቆ ስለመሄዱም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ከነዋሪው በቀር ጅጅጋ ባዶዋን ናት። ማንም የሚጠብቃት ሰው አልነበረም።

የሱማሌ ታንከኛ ጦርም በኢትዮጵያ አየር ኃይል እንዳይመታ በመስጋት በቀን ወደ ከተማው ለመግባት አልደፈረም። ከአምላኳ በቀር ሌላ ጠባቂ ያልተረፈላት የጅጅጋ ከተማ እስከ ምሽት ድረስ፤ አጭር እድሜ አላት። የመንግስት ባለስልጣና እና ወታደሩ አካባቢውን ለቅቆ ወጥቷል።

ጀንበር ስትጠልቅ፤ የሱማሌ ጦር ወደ ጅጅጋ ገብቶ የነበረው እንዳልነበረ ይሆናል። በዚህ የመጨረሻ የጭንቅ ሰዓት አንዳንድ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ ጦር ሰፈር ገብተው የቻሉትን ያህል መሳሪያ ወስደው ራሳቸውን ለመከላከል ታጠቁ። የኢትዮጵያ ጦር የሚለብሰውን የወታደር ልብስ ለብሰው፤ ጠመንጃቸውን አንግተው... በታንክ የመጣውን የሱማሌ ጦር ለመዋጋት ተዘጋጁ። ፈይሳ ጃታ በዚህ ሁኔታ የጅጅጋን ህዝብ የሚያስተባብሩ ብቻ ሳይሆን፤ ለዚያን ቀን ከመንግስት ያልተሾሙ፤ የጅጅጋ ህዝብ መሪ ሆኑ።

ፈይሳ ጃታ... በዚያች ቀውጢ ወቅት መሪነታቸውን አስመሰከሩ። በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከሰው ባልተናነሰ መልክ፤ ሰንደቅ አላማ ትልቅ ክብር ስለሚሰጠው "ሰንደቅ አላማ በጠላት እጅ መውደቅ የለበትም።" በማለት፤ በቅድሚያ በጅጅጋ አስረኛው ሜካናይዝድ ብርጌድ ግቢ ውስጥ የተሰቀለውን የኢትዮጵያ ባንዲራ አወረዱ። ለአገራቸው ክብር የኢትዮጵያ ወታደር ልብስ የለበሱት ፈይሳ ጃታ ይህችን ሰንደቅ አላማ ይዘው፤ ህዝቡን እያረጋጉ፤ ወጣቱን እያስተባበሩ ወደ ሃረር ጉዞ ጀመሩ። ሆኖም የሃረር መንገድ ተዘግቷል። ከሃረር አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ... ከመቶ ሺህ ህዝብ በላይ ከካራማራ ተራራ ጀርባ፤ ሀደው ከተማ ላይ ሰፍሯል።

ከሃደው ከተማ የተነሳው ህዝብ ቀስ በቀስ ወደ ሃረር መሄድ ቢጀምርም፤ የሚደረገው ጉዞ አስቸጋሪ ነበር። በየጋራው ላይ የመሸገውን የሱማሌ ጦር እየተዋጉ መሄድ ግድ ይላል። ፈይሳ ጃታ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ጦር መትረየሳቸውን ደግነው፤ እየተኮሱና እየተዋጉ ጉዞ ወደ ሀረር ሆነ። ከጅጅጋ ወደ ሃረር የነበረው ጉዞ ከ25 ቀናት በላይ ፈጀ። የኢትዮጵያ አየር ኃይል በሰማይ ሲያንዣብብ፤ የሱማሌ ጦር የሚገባበት ስለሚጠፋው... በዚያች አጋጣሚ ህዝቡ ከየመሸገበት እየወጣ ወደ ሃረር የሚያደርገውን ጉዞ በፍጥነት ይቀጥል ነበር።

የሃረር ህዝብ እንዳይደነግጥ ስለተሰጋ፤ ከጅጅጋ እና ከኦጋዴን ከተሞች የፈለሰው ህዝብ ወደከተማው እንዲገባ የተደረገው ለሊት ላይ ነበር። የሃረር ህዝብ ግን ቀደም ብሎ መስማቱ አልቀረም። ፈይሳ ጃታ ሃረር ወደሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው ሲሄዱ፤ ልጆቻቸው የደርግ ተቃዋሚ ተብለው ቀበሌ እንዳሰራቸው ይሰማሉ። በሱማሌ ወረራ ጅጅጋ ላይ የተመለከቱት ውርደት ሳያንስ፤ ሃረር ውስጥ ልጆቻቸው መታሰራቸውን ሲሰሙ በቀጥታ ወደ ቀበሌ ሄደው አብዮት ጠባቂውና ሊቀመንበሩ ላይ አነጣጥረው፤ "ሱማሌ 45 ኪሎ ሜትር ላይ ቁጭ ብሏል። እናንተ መንደር ለመንደር ትበጠብጣላቹህ። ፍቷቸው!" ብለው ሲጮሁ ሚስታቸው፤ "አረ ይተዉ። የታሰሩት የርስዎ ብቻ አይደሉም፤ የሁሉም ልጆች ናቸው እኮ" ቢሏቸው... "አሁን የአገር ጉዳይ ነው። አገር እየተገደለች እና እየተዋረደች ልጆቻችን እንደገና በእስር አይንገላቱም። ፍቷቸው!" በማለት ሁሉም ታሳሪ እንዲፈቱ አደረጉ። (በወቅቱ ከታሰሩት ልጆቻቸው መካከል አንዳንዶቹ አውሮፓ ውስጥ ናቸው)

ፈይሳ ጃታ በዚህ አይነት ሃረር ላይ ከቆዩ በኋላ፤ አንድ ቀን ሌላ ችግር ገጠማቸው። የወታደር ልብስ፣ ጫማ ወይም መለዮ መልበስ በአዋጅ ተከልክሏል። ሆኖም ፈይሳ ጃታ አላግባብ የወታደሩን ልብስ በመልበሳቸው ታሰሩ።። ታስረም የሃረር ክፍለ አገር አስተዳዳሪ ከነበረው ኮሎኔል ዘለቀ በየነ ዘንድ ቀረቡ። እዚያም ቀርበው፤ የወታደሩን ልብስ መልበሳቸው ትክክል እንዳልሆነ እና ወንጀል የፈጸሙ መሆኑ ተነገራቸው።

ፈይሳ ጃታም የባለስልጣናቱን ውንጀላ ከሰሙ በኋላ፤ "ይህን የወታደር ልብስ እኔ ብቻ አይደለም የለበስኩት። ይህንን መለዮ እና ልብስ ትታችሁ የሸሻችሁት እናንተ ናቹህ፤ ይህን ልብስ በየቦታው በመተዋቹህ የሱማሌ ጦር ጭምር ለብሶታል። እኔ እናንተ ትታችሁ የሄዳችሁትን ልብስ በመልበሴ እወንጀል ይሆናል። እናንተ ደግሞ ልብስ እና መሳሪያዎችን ትታችሁ ሱማሌ እንዲወስደው በማድረጋቹህ፤ አንድ ቀን ትጠየቃላቹህ።" አሏቸው።

በዚህ ጉዳይ አንድ ሁለት እያሉ ሲከራከሩ፤ ፈይሳ ጃታ በመጨረሻ የሰንደቅ አላማውንም ጉዳይ ነገሯቸው። "እናንተ የልብሱ ጉዳይ ለምን ይገርማችኋል? ከ10ኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ግቢ የተዋችሁትን ሰንደቅ አላማ ጭምር፤ በስርአት አውርጄ ይዤው መትቻለሁ።" አሏቸው። ይህ አባባል ሁሉንም ዝም አሰኘ። ማንም መልስ ለመስጠት አልሞከረም። ኮሎኔል ዘለቀ በየነም፤ የፈይሳ ጃታን ጀግንነት አድንቀው እንዲፈቱ ትዕዛዝ ከመስጠት ውጪ ምንም አላሉም።

ጊዜው በግርግር እና በጦርነት እሳት ተወጥሯል። የኢትዮጵያ ጦር ተጠናክሮ እንደገና ማጥቃት ጀመረ። ከአስር ወራት በኋላ፤ የሱማሌ ጦር ከአካባቢው ሙሉ ለሙሉ ተደምስሶ ጅጅጋ እንደገና በኢትዮጵያ አስተዳደር ስር ወደቀች። ሀረር ላይ ሰፍሮ የነበረው ህዝብ እንደገና ወደ ጅጅጋ ከተማ ተመለሰ። እነሆ የድል ምስራች ከዳር እስከ ዳር አስተጋባ።

ፈይሳ ጃታ እና ተከታዮቻቸው ወደ ጅጅጋ ከተማ ሲመለሱ፤ ህዝቡ እንዳጀባቸው በቀጥታ ያመሩት ወደ ቤታቸው አልነበረም። ከአስር ወራት በፊት በክብር ያወረዱትን ሰንደቅ አላማ በክብር መልሰው ለመስቀል ወደ 10ኛው ሜካናይዝድ ብርጌድ ግቢ አመሩ። ወታደሩም አስተዳደሩም፣ ህዝቡም አጀባቸው። የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማን በታላቅ ክብር፤ በደስታና በሆታ መልሰው ሰቀሉ።

ከዚህ በኋላ ፈይሳ ጃታ ወደ ቤታቸው ተመልሰው የወታደር ልብሳቸውን አወለቁ። የዚህ ታሪክ ተራኪም ከጥቂት ቀናት በኋላ ኢትዮጵያን ለቅቆ ስለወጣ፤ ስለፈይሳ ጃታ በወሬ በወሬ ከሚሰማው በቀር፤ ቀሪ ታሪካቸውን አያውቅም። ሆኖም በታሪክ ስማቸውን ከፍ የሚያደርግ ብሄራዊ ውርደትን አልቀበል ብለው እንደተፋለሙ ጠንቅቆ ያውቃል። በመጨረሻም በእርጅና ቆይተው አስከሬናቸው ሃረር ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በክብር ማረፉን ሲያወራ፤ ለሱም ክብር ይሰማዋል።

ዛሬ የምንሰማው "ብሄራዊ ውርደት" በየትኛውም ዘመን እና ወቅት፤ በየትኛውም መንደር እና አገር ሊያጋጥም ይቻላል። ዋናው ቁም ነገር... ይህንን ውርደት የሚሸከም ህሊና የሌለን መሆኑን ማረጋገጡ ላይ ነው። ይህንን የምናረጋግጠው ደግሞ በወሬ ብቻ ሳይሆን፤ እንደ ፈይሳ ጃታ ለኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ እና ለህዝብ ክብር በመቆም ነው!!